የሰ.መ.ቁ.181512

መስከረም 25 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፊይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት - ዐ/ሕግ ተክለ ልብሰወርቅ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- ቴክኒካል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

1. ሚ/ር አንድሬ ፔሽዲማልጂ ⎫ ዶ/ር ያሬድ ለገሰ - ቀርበዋል

2. ሚ/ስ ሞኒክ ፔሽዲማልጂ ⎭

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍ ር ድ

ይህ ወራሽ የሌለዉ የዉርስ አክስዮን ድርሻ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.167717 ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ ቴክኒካል ትሬድንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ፣ እና በአሁን ተጠሪዎች የተቋቋመ ማህበር ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪዎች በማህበሩ ዉስጥ እያንዳንዳቸዉ የነበራቸዉን 10% የአክስዮን ድርሻ ለማህበሩ አባል ለሆነዉ ለሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ እያንዳንዳቸዉ በብር 375,000 በጠቅላላዉ በብር 750,000 የሸጡና የሽያጭ ገንዘቡን የተቀበሉ መሆናቸዉን የማህበሩ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ የሚያረጋግጥ ስለሆነ፣ ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ በመሞታቸዉና ወራሾች ባለመኖራቸዉ የአሁን ተጠሪዎች በማህበሩ ዉስጥ ምንም ዓይነት መብት የሌላቸዉ ስለሆኑ ማህብሩ እንዲፈርስ፣ የሟች ድርሻ ወራሽ የሌለዉ ሀብት ስለሆነ ለመንግስት እንዲተላለፍ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ የአክስዮን ዝዉዉር የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተጠቀሱትን የማህበሩን አባላት መለወጥን ስለሚያስፈልግ ይህ ደግሞ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 334/1995 እና 922/2008 መሰረት በዚህ ጽ/ቤት የተፈረመ የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ስለሌለ በአሁን ተጠሪዎች የተመዘገቡት አክስዮኖች ተሸጠዋል በማለት የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ተቀባይነት የለዉም፤ የአሁን አመልካች ያቀረባቸዉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች የሚያሳዩት የአሁን ተጠሪዎች ገንዘቡን የተቀበሉት ገዢ ነዉ ከተባለዉ ከሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ ሳይሆን ከማህበሩ ከራሱ በመሆኑ ወደፊት ከማህበሩ ከሚደርሰን የትርፍ ድርሻ የሚታሰብ ነዉ እንጂ የአክስዮን ዝዉዉር የሚያሳይ አይደለም፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የአክስዮን ድርሻቸዉን ለሚ/ር ክላዉዲዮ ማሪኖ በሽያጭ ስለማተላለፋቸዉ የቀረበ የአክስዮን ሽያጭ ዉል እና ከግለሰቡ ገንዘብ መቀበላችንን የሚያስረዳ ማስረጃ የቀረበ ነገር የለም፡፡ አንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባል ሲሞት እና ወራሾች የሚቹን የአክስዮን ድርሻ አንፈልግም ካሉ ይህ ማህበር ካለዉ ልዩ ባህርይ አንጻር የአክስዮን

ድርሻዉ ወራሽ እንደሌለዉ የዉርስ ሀብት ተቆጥሮ ለመንግስት የሚተላለፍበት አግባብ የሌለ እና ለተቀሩት የማህበሩ አባላት እንደየድርሻቸዉ የሚደለደል ይሆናል። ስለሆነም ሟች በዚህ ማህበሩ ዉስጥ የነበረዉ የአክስዮን ድርሻ ለአሁን ተጠሪዎች መደልደል አለበት እንጂ ለመንግስት የሚተላለፍ አይሆንም። እነዚህ ክርክሮቻችን ታልፈዉ መንግስት የማህበሩ አባል ይሆናል የሚባል ከሆነ ማህብሩ አሁንም በሕግ የተመለከተዉ አነስተኛ የአባላት ቁጥር የሚያሟላ ስለሆነ ማህብሩ በዚህ ምክንያት የሚፈርስበት አግባብ የለም የሟች የአክስዮን ድርሻ ለአሁን ተጠሪዎች ሊደለደል ይገባል፤ በአማራጭ የአሁን አመልካች በማህበሩ ዉስጥ በሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ ስም የተከፈለዉን የአክስዮን ገንዘብ ተከፍሎት በማህበሩ ላይ ተጨማሪ ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮችን በመስማት እና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን ተጠሪዎች በማህበሩ ዉስጥ በስማቸዉ የተመዘገቡትን አክስዮኖች ለሚ/ር ክላዉዲዮ ማሪኖ ለመሸጣቸዉ የሚያስረዳ የአክስዮን ሽያጭ ዉልም ሆነ ሌላ የጽሑፍ ማረጋገጫ ያልቀረበ ሲሆን፣ አክስዮን ዝዉዉር ደግሞ የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ መለወጥን ማሻሻልን ስለሚያስከትል በአዋጅ ቁጥር 334/1995 አንቀጽ 5 እና በአዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 9 [1፣ ሐ] መሰረት በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ሲፈረምና ሲረጋገጥ ብቻ በመሆኑ በዚህ አግባብ የቀረበ ነገር የለም። የአሁን አመልካች ያቀረበዉ የክፍያ ሰነድ ለአሁን ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸዉ ብር 375,000 በቅድሚያ ክፍያነት ከማህብሩ የተከፈላቸዉ ነዉ እንጂ የአክስዮን ዝዉዉር የሚያሳይ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በሻጭና በገዢ የተፈረመ ቃለ ጉባኤና የሽያጭ ዉል አይደለም። የአሁን ተጠሪዎች ይህን ከማህበሩ የተቀበሉትን ገንዘብ ወደ ፊት ከማህበሩ ከሚደርሳቸዉ የትርፍ ድርሻ የሚታሰብ ነዉ ከሚባል በስተቀር የአክስዮን ዝዉዉር የሚያሳይ አይደለም።

ይህ ማህበር በሶስት አባላት የተቋቋመ ማህበር በመሆኑ ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ በመሞቱ የማህበሩ አባላት ሁለት በመሆናቸዉ በሕግ የተቀመጠዉን አነስተኛ የአባላት ቁጥር የሚያሟላ ስለሆነ አንዱ አባል በመሞቱ ማህበሩን የሚያስፈርስ ባለመሆኑ ማህበሩ ሊፈርስ አይገባም።

የማህበሩ አባል የሆነዉ ሚ/ር ክላዉዲዮ ማሪኖ በመሞቱ የሟቹ ወራሾች የውርስ ሀብት የሆነዉን በሟች ስም ተመዝግቦ የሚገኙት የአክስዮኖች ድርሻ አንፈልገዉም በማለታቸዉ የሟች የአክስዮን ድርሻ ምን መሆን አለበት የሚለዉ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 524 [1]፣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.995 እና 852 መሰረት ለዉርስ ሀብት ማስተላለፍ ዓላማ ሲባል ሟች ዘመዶች እንደሌሉት ተቆጥሮ የአክስዮን ድርሻዉ ወራሽ እንደሌለዉ የዉርስ ሀብት ሊቆጠርና ለመንግስት ሊተላለፍ ይገባል። ይሁን እንጂ መንግስት ከተቋቋመበት ሚና እና ከማህበሩ ዓላማ አንጻር ሲታይ መንግስት የማህበሩ አባል ሆኖ መቀጠል ስለማይችል አሁን ማህበሩ ያለበት አቋም ተጣርቶ የሟች የአክስዮኖች ድርሻ አክስዮኖቹ ወቅታዊ ዋጋቸዉ ተለይቶ በሚገኘዉ የአክስዮኖች ዋጋ ልክ የአሁን ተጠሪዎች ለአሁን አመልካች እንዲከፍሉ ክፍያዉ ሲፈጸም የሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ አክስዮኖች ለተጠሪዎች በድርሻቸዉ መጠን እንዲደለደሉ በማለት ወስኗል።

የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ማህበር ዉስጥ ሟች ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ የአክስዮን ድርሻ 80%፣ የአሁን ተጠሪዎች እያንዳንዳቸዉ 10% ሲሆን፣ የሟች የዉርስ ሀብት ለመንግስት የሚተላለፈዉ ሟቹ ዘመዶች የሌሉት መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.852 ሥር የተደነገገ ሲሆን፣ በዚህ ጉዳይ ሟች ዘመዶች የሌሉት ሳይሆን ዘመዶች ኖሮት ወርሱን እንደማይፈልጉ የተረጋገጠ ስለሆነ ይህ ከሆነ ደግሞ የሟቹ የዉርስ ሀብት ለመንግስት እንዲተላለፍ የሚያስችለዉ የህጉ መስፈርት [ሟች ዘመዶች የሌለዉ የመሆኑ ጉዳይ] ባልተሟለበት ሁኔታ የአሁን አመልካች ከጅምሩ ይህ ለክርክር መነሻ የሆነዉ የዉርስ ንብረት ለመንግስት ሊተላለፍ ይገባል የሚለዉን ዳኝነት ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችለዉ መብትና ጥቅም የለዉም በማለት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ።

የአሁን አመልካች በ23/11/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የሥር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር “አመልካች ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለዉም” በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ባላነሱበት አዲስ የክርክር ነጥብ በራሱ በማንሳት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.329 [1] መሰረት ያላስረዳ ስለሆነ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። የሥር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የማህበሩ አባል ሞቶ እያለ የሟች የአክስዮን ድርሻ ለመንግስት አይተላለፍም ማለቱ በዉጤት ደረጃ አክስዮኖቹ ለቀሪ ባለአክስዮኖች ለሆኑት ለአሁን ተጠሪዎች እንዲደለደል የሚያደርግ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። የሟች ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ አክስዮኖችን በንግድ ሕግ ቁጥር 524 በደንቡ ለወራሾች እንዳይተላለፍ ወራሾች የሆኑት መዉረስ አንፈልግም ያሉ በመሆናቸዉ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.995 እና 852 አንጻር ሲታይ እስካሁን ድረስ ዉርስ ይገባኛል ሲል ዳኝነት የጠየቀ ባለመኖሩ፣ የሟችን የዉርስ ሀብት የማይመለከተዉ ሌላ ሰዉ እንዳይወስድ እና እንዳይጠፋ ለማድረግ ለዉርስ ማስተላለፍ ዓላማ ሲባል ብቻ ሟች ዘመዶች [ወራሾች] እንደሌሉት በመቁጠር የዉርስ ሀብቱ ለመንግስት መተላለፍ ያለበት ሆኖ ሳለ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። ስለሆነም የሥር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲሻርልን፣ ሟች በቴክኒካል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ዉስጥ ያለዉን 80% የአክስዮን ድርሻ ወራሽ እንደሌለዉ የዉርስ ሀብት ተቆጥሮ ለመንግስት እንዲተላለፍ ዳኝነት የመጠየቅ መብትና ጥቅም ያለዉ በመሆኑ የዉርስ ሀብት ለመንግስት መተላለፍ አለበት ተብሎ እንዲወሰንልን።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሟች ወራሾች የሟችን የአክስዮን ድርሻ መዉረስ አንፈልግም ቢሉም የሟች የአክስዮን ድርሻ ለመንግስት አይተላለፍም፣ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.852 አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት ታህሳስ 13 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የሟች ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ የአክስዮን ድርሻ ለመንግስት ሊተላለፍ ይገባል በማለት ዳኝነት ለመጠየቅ መብትና ጥቅም የለዉም ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በሥር ፍ/ቤቶች ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር መገንዘብ እንደሚቻለዉ ቴክኒካል ትሬድንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በሶስት አባላት በሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ እና በአሁን ተጠሪዎች የነበሩት መሆኑን የማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ የሚያሳይ ሲሆን፣ ታህሳስ 15 ቀን 2003 ዓ.ም የተጻፈ ቃለ ጉባኤ የማህበሩ አባላት የአክስዮኖችን ድርሻ የሚጠቁም ሆኖ ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ 80%፣ የአሁን ተጠሪዎች እያንዳንዳቸዉ 10% የአክስኖች ድርሻ እንዳላቸዉ የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ እና ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሚ/ር ክላዉዲዮ ማሪኖ በዜግነት ጣሊያናዊ ሲሆን ሐምሌ ወር 2003 ዓ.ም ከዚህ ዓላም በሞት ተለይተዉ በሚኖርበት በጣሊያን አገር እንደተቀበረ የአሁን አመልካች በክሱ ላይ የገለጸዉን ፍሬ ነገር የአሁን ተጠሪዎች በማስተባበል የተከራከሩ ነገር መኖሩን የሥር ፍ/ቤት መዝገብ አያሳይም። ስለዚህ ሚ/ር ክላዉዲዩ በ2003 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆናቸዉን መገንዘብ ተችሏል። ሚ/ር ክላዉዲዩ በመሞቱ በዚህ ማህበር ዉስጥ በስሙ ተመዝግቦ የሚገኙት የአክስዮኖች ድርሻ በተመለከተ የሟች ወራሾች የዉርስ አክስዮን ድርሻ መዉረስ እንደማይፈልጉ በአካልም በኢ.ሜይል እንደገለጹ የአመልካች የሰዉ ምስክሮች መመስከራቸዉ፣ የአሁን ተጠሪዎችም ይህን ፍሬ ነገር በመቀበል የሟች ወራሾች የዉርስ የአክስዮን ድርሻ መዉረስ አንፈልግም ማለታቸዉን በመግለጽ የተከራከሩ

ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ እንዳረጋገጡት የሟች የዉርስ አክስዮን ድርሻ ዉርስ የተገባቸዉ ወራሾች መዉረስ አንፈልግም ማለታቸዉን በማረጋገጥ ዉሳኔ ሰጥቶበታል። ስለሆነም በሟች ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ ስም በዚህ ማህበር ዉስጥ ተመዝግቦ የሚገኙትን የአክስዮኖችን ድርሻ "የሟች ወራሾች መዉረስ አንፈልግም" ማለታቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ። ይህ ከሆነ ሟች ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ በዚህ ማህበር ዉስጥ ያለዉ የአክስዮኖች ድርሻ ምን መሆን አለበት? የሚለዉ አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር ማየቱ ተገቢ ነዉ።

ከዚህ አንጻር የንግድ ሕግ አንቀጽ 524 [1] መሰረት በመተዳደሪያ ደንብ በሌላ አግባብ ካልተነገረ በቀር የአንድ ማህበር አባል ወራሾች ለሟቹ አክስዮኖች በደንብ ወራሾች እንደሚሆን ይደነግጋል። ነገር ግን የንግድ ሕጉ ወራሾች እነማን ናቸዉ? ለሚለዉ ጥያቄ ምላሽ የሚሳጥ ስላልሆነ በዚህ ሕግ አንቀጽ 1 መሰረት የፍትሀ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንዳላቸዉ ስለሚያመለክት አንድ የማህብር አባል ሲሞት ወራሾች ማን ናቸዉ? ለሚለዉ ጥያቄ ከዚህ ሕግ ምላሽ ማግኘት የሚቻል ይሆናል። ስለሆነም አንድ ሰዉ ኑዛዜ ሳያተርፍ የሞተ እንደሆነ የሟች ወራሾች የሚባሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.842 መሰረት የመጀመሪያ ዝምድና ደረጃ ያላቸዉ የሟቹ ልጆች፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.843 መሰረት ሁለተኛ የዝምድና ደረጃ ያላቸዉ የሟቹ አባትና እናት፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.845 መሰረት ሶስተኛ የዝምድና ደረጃ ያላቸዉ የሟች አያቶች፣ እነዚህ ከሌለዉ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.847 መሰረት አራተኛ የዝምድና ደረጃ ያላቸዉ የሟቹ ቅድመ አያቶች ወራሾች እንደሚሆኑ ተደንግጓል። እንዲሁም ሟች በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ወራሾች የሚሆኑት ዘመዶች የሌሉት እንደሆነ ሕጉ ምላሽ መስጠቱን መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.852 መሰረት ዘመዶች የሌሉ እንደሆነ የሟቹ ሀብት ወራሽነት ለመንግስት እንደሚተላለፍ ደንግጓል። በዚህ ድንጋጌ "የሟች ዘመዶች" የሚባሉት ከፍ ሲል በተጠቀሱት ደንጋጌዎች መሰረት በቅደመ ተከተሉ መሰረት በሕጉ አግበብ የሟች ወራሾች ሊሆኑ የሚችሉትን ሰዎች እንደሚያመለክት ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል።

ሟች ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ ወራሾች የሌሉት ሳይሆን ወራሾች እያሉ የዉርስ ሀብት የሆነዉን የአክስዮን ድርሻ ለመዉረስ አንፈልግም ማለታቸዉን ከፍ ሲል ተመልክተናል። ይህ ከሆነ የሟች ወራሾች በማህበሩ ዉስጥ በሟች ስም ተመዝግቦ የሚገኙትን የአክስዮኖች ድርሻ አንፈልግም ማለታቸዉ ዉጤቱ ምን ይሆናል? የሚለዉ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ። ይህ ጉዳይ ሲታይ የሟቹ ወራሾች የዉርስ ሀብት የሆነዉን የአክስዮኖች ድርሻ ለመወረስ አንፈልግም፣ አንቀበልም ማለታቸዉ ዉርስ የተዉ መሆናቸዉን ያስገነዝባል።

እንደሚታወቀዉ ወራሽነትን መቀበል ወይም አልቀበልም የማለቱ ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.976 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የሚመራ ነዉ። በፍ/ብ/ሕ/ቁ.977 [1] መሰረት ወራሽነትን የመቀበል ወይም አልቀበልም የማለት ፈቃድ የወራሹ የራሱ መብት ብቻ ነዉ። አንድ ወራሽ ወራሽነት ተቀብያለሁ ወይም ለቅቃለሁ [ትቻለሁ] ያለ እንደሆነ ሁለቱም የየራሳቸዉ ዉጤት እንዳላቸዉ ከሕጉ መገንዘብ ይቻላል። ወራሽነቱን ትቻለሁ የሚል ወራሽ መቼዉንም ወራሽ እንዳልሆነ እንደሚገመት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.995 [1] ሥር ተመልክቷል። ወራሽ አልፈልግም ያለዉን ድርሻ በተመለከተ ወራሽነቱን ለተቀበሉት ለአብሮ ወራሾች አስፈላጊም ሲሆን ለተከታይ ወራሾች የሚተላለፍ መሆኑን የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 2 ያስገነዝባል።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሟች ሚ/ር ክላዉዲዮ ማሪኖ ወራሾች የዉርስ ሀብት የሆነዉን በሟች ስም ተመዝግቦ የሚገኙትን የአክስዮኖች ድርሻ ወራሽነት አንፈልግም ማለታቸዉ ተረጋግጧል። የሟች ወራሽነት የተቀበሉ አብረዉ ወራሾችም የሆኑ ተከታይ ወራሾች እስካሁን ድረስ የሟቹን የአክስዮኖች ድርሻ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.995 [3] መሰረት እንቀበላለን ብለዉ የቀረቡት ወራሾች እንደሌሉ የሥር ፍ/ቤት መዝገብ እና እስከዚህ ችሎት የተደረገ የግራ ቀኙ ክርክር ያሳያል። ይህ ማለት የሟች ወራሾች የተባሉት ሁሉ የዉርስ ሀብት የሆነዉን የአክስዮኖችን ድርሻ አንፈልግም ማለታቸዉን የሚያስገነዝብ ነዉ። ይህ ከሆነ ደግሞ እነዚህ ወራሾች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.995 [1] መሰረት ወራሽነትን አንፈልግም በማለታቸዉ የሟቹ ወራሾች እንዳልሆኑ ይቆጠራሉ ማለት ነዉ። እነዚህ ወራሾች ደግሞ የሟቹ ወራሾች እንዳልሆኑ ከተቆጠሩ፣ ሟች ከፍ

ሲል በተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች ሥር የተመለከቱትን ሟቹን ለመዉረስ በሕግ የተገባቸዉ ከመጀመሪያ የዝምድና ደረጃ እስከ አራተኛ የዝምድና ደረጃ ያሉት ወራሾች የሚሆኑት ዘመዶች አለመኖራቸዉን የሚያመለክት ነዉ፡፡ ሟቹን የሚወርሱ እስከአራተኛ የዝምድና ደረጃ ያሉት ወራሾች ከሌሉ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.852 መሰረት እልባት ሊሰጠዉ የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ ደንጋጌ መሰረት ሟች ዘመዶች የሌሉት እንደሆነ ሕጉ ምላሽ ሰጥቶበት እናገኛለን፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.852 መሰረት ዘመዶች የሌሉ እንደሆነ የሟቹ ሀብት ወራሽነት ለመንግስት ይተላለፋል የሚል ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የሟቹ ሚ/ር ክላዉዲዩ ማሪኖ የዉርስ ሀብት የሆነዉ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ማህበር በስሙ ተመዝግቦ የሚገኙት የአክስዮኖች ድርሻ የሚወርስ ዘመድ የሌለዉ የዉርስ ሀብት ስለሚሆን  የዉርስ ሀብቱ መተላለፍ ያለበት ለመንግስት ነዉ እንጂ በዚህ ሁኔታ ከመንግስት የተሻለ መብትና ጥቅም ያለዉ አካል ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ሟቹ ሚ/ር ክላዉዲዮ ማሪኖ የአክስዮኖች ድርሻ 80% ሊተላለፍ የሚገባዉ ለመንግስት ለአሁን አመልካች እንጂ ይህ የዉርስ ሀብት በሕግ ይገባኛል መብትና ጥቅም አለኝ የሚል ሌላ አካል የለም፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ አግባብ ሕጉን በአግባቡ በመተርጎም የአሁን ተጠሪዎች የሟቹን የአክስዮኖች ድርሻ በወቅታዊ ዋጋቸዉ ለአመልካች ከፍለዉ ለእነርሱ እንዲደለደል በማለት የሰጠዉን ዉሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመሻር የአሁን አመልካች ይህን ክስ አቅርቦ ዳኝነት የመጠየቅ መብት የለዉም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የሟቹ የዉርስ ሀብት የሆነዉ የአክስዮኖች ድርሻ ለመንግስት ሊተላለፍ ይገባል በማለት ዳኝነት ለመጠየቅ መብትና ጥቅም እያለዉ የለዉም በማለት የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት በሕጉ አግባብ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የወሰነዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.167717 ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.177921 በ27/11/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. የመ.ቁ.177921 የሆነዉ መዝገብ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይመለስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞችፊርማ አለበት

ሰ/ጥ